የሰበር መ/ቁ. 24577

ቀን ሰኔ 20 ቀን 1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. " ጌታቸው ምህረቴ

4. " መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢ.ት.መንገዶች ባለሥልጣን ጅማ ዲስትሪክት

መልስ ሰጭ፡- ባዩሽ ዘየገ

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ(ን) ይወሰንልኝ(ን) የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት/cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የሕግ ነጥብ የሚመለከት ነው፡፡

ምሥራቅ ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ መ/ሰጭ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ በመቀበል አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ከላይ የተመለከተውን የሕግ ነጥብ ሳይመረመር አልፎታል፡፡

አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልስ ሰጥቷል፡፡

ችሎቱም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ(ን) ይወሰንልኝ(ን) የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /Cause of action/ አለው? ወይስ የለው? የሚለውን የሕግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበትን ውሣኔ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 16273 ጥቅምት 22 ቀን 1998 በሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች በመተርጎም አንድ ሰራተኛ ከውሉና ከአሰሪና ሠራተኛ ሕጉ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 26/10/98

አንፃር ሊያገኘው የሚገባና የቀረበለት ጥቅም ካለ የቀረበት ጥቅም እንዲሰጠው መጠየቅ /ክስ ማቅረብ/ የሚችል ሲሆን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ ብቻ የሚቀርብን ክስ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድም ሆነ የስራ ክርክር ችሎት ተቀብለው ሊያዩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በዚህ ጉዳይም ም/እ/አ/ሠ/ወሣኝ ቦርድ መ/ሰጭ ያቀረቡትን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ማድረግ የነበረበት ሲሆን ጉዳዩን ተቀብሉ በማከራከር ውሣኔ በመስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል።

## ው ሣ ኔ

ም/አ/አ/ሠራተኛ ወ/ቦርድ በመ.ቁ.ቢ-ኤም 20-64 2557 የሰጠው ውሣኔና የአ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28271 የሰጠው ትእዛዝ /ውሣኔ/ ተሽሯል።

- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ።
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 26-10-98